22110013

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Wednesday 11 May 2011 (morning)
Mercredi 11 mai 2011 (matin)
Miércoles 11 de mayo de 2011 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.




© International Baccalaureate Organization 2011

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።*

**1.**

ታላቁ ምቾት ይከተለዋል። ልዩነት ነበረን፤ የእናቴ እናት /እማማ በረኩት/ “የልጅ ልጄ ሳይሰለቸው አይቀርም” ብለው፤ ከአንድ ሰዓት በላይ የእግር መንገድ ተጉዘው እንጀራ ገዝተው ያበሉት ነበር። የእናቴ አባት ደግሞ “ቄየግ” ይጫወቱለት ነበር። “ቄየግ” ያላንዳች የሙዚቃ መሳሪያ ቅንብር፣ ጀግኖች የሚወደሱበት፣ ጉዛው ለራሱ ሰዎች ያለውን ክብር የሚያስደምጥበትና ማህበረሰቡ የሚነቃቃበት ዘፈን ነው።

ከእናቴ ቤተሰቦች ፊት ለፊት አንድ የ“ፉጋ” ቤተሰብ አለ። የእናቴ ቤተሰቦች ስራ ሲበዛባቸው እነዚህ ፉጋዎች ናቸው ሸክማቸውን የሚያቀልሉላቸው።

ፉጋዎች በአካባቢው ተወላጆች ዘንድ የተናቁ ናቸው ይባላል። ቡና እንዲጠጡ ሲጋበዙ የራሳቸውን ስኒ ነው ይዘው የሚመጡት። ስኒያቸው ከሌሎች ስኒዎች ጋር አይደባለቅም። እነሱ በጠጡበት ስኒ ቡና የሚጠጣ የለም። እነሱ ቡና ካፈሉ የሚጋብዙትም ሆነ የሚጋበዝላቸው ሰው የለም። ሰውን ወደየቤታቸው የማይጠሩት የሚመጣላቸው ሰው ስለሌለ ነው ብለውኛል።

… አባወራው ፉጋ ለአንድ ሁለት ወራት ያህል የት እንደሄደ፣ ለምን እንደሚሄድና መቼ እንደሚመለስ ለሚስቱም ሆነ ለልጆቹ ሳይናገር ይጠፋል። ከሄደበት ሲመለስ “የት ጠፍተህ ነው?” ብለህ ትጠይቀዋለህ። እሱም “አንዲት ባልዋ የምተባት ዘመዴን ልጠይቅ ሄጄ ነው” ይልሃል።

“እና – ጠይቀሃት መጣህ?!”

“አግብቻት መጣሁ እንጂ፤ ከኔ በላይ የሚቀርባት ዘመድ ሳይኖር ሲቀር እኔ አገባሁዋት!” ይልሃል። ይሄ የፉጋዎች ልማድ ነው።

… ደርግ ነው ከሰው እኩል ያደረገን ይላሉ። እኩል ነን ብለው ግን አያምኑም። ከደርግ ዘመን በፊት፣ ከየባለሀብቱ ጓሮ ግርጌ ነበር የሚሰፍሩት። የራሳቸው የሆነ መሬት አልነበራቸውም የምትኖራቸውም ደሣሣ ቤት – እንደዘበት ተገንብታ እንደዘበት መፍረስ የምትችል ጎጆ።

ይሰራሉ፤ የባለ ሀብቱን ንብረት ይጠብቃሉ፤ ያርሣሉ፤ ይኮተኩታሉ። እንዲህ ነበር አኗኗራቸው። ደርግ መጥቶ፣ አብዮት ፈንድቶ የማያውቁትን አለም አሣያቸው። “ከማንም አታንሱም፤ ማንንም አትበልጡም” አለና፤ ከጓሮ አውጥቶ ደጅ ላይ አስቀመጦ አስደነገጣቸው። ድንጋጤው አሁንም ቢሆን በልጆቻቸውና በልጅ ልጆቻቸው ላይ ተባዝቶ አየዋለሁ።

በቀርከሃ የሚሰሩ የመዝጊያ በሮችን፣ ሳጠራዎችንና ሌሎች የማዕድ ቁሣቁሶችን አበጅተው በመሸጥ ነው የሚተዳደሩት። ፉጋዎች ዛሬን ብቻ በልቶ፣ ጠጥቶና ተደስቶ ስለመኖር ነው ግድ የሚሰጣቸው፤ ሀብት የማደርጀት ልምድ የላቸውም ሲባል እሰማለሁ።

… አምላክ ድሮ ምድር ላይ ይኖር ነበር አሉ – ከሰው፣ ከአራዊት፣ በባህርና በየብስ ከሚኖሩት ጋር። አንድ ቀን ድካም ተሰምቶት ዛፍ ስር ተቀምጦ እረፍት እያደረገ ሳለ ሸለብ ያደርገዋል። የፉጋዎች አባት፣ የእለቱን የእርሻ ውሎ አጠናቅቆ ወደቤት በመግባት ላይ ነበር። ከዚያ ዛፍ ስር እያለፈ ነበርና አምላኩን አየው። ተኝቷል አርቃኑን ነው። ሰውነቱ ተገላልጧል። የአምላክ እንዲህ መገላለጥ ሣቁን አመጣበትና፣ የሣቀበትን ጉዳይ ለወንድሞቹ ለመናገር ተሸቀዳደመ። ነገራቸውም።

ወንድሞቹ ግን እሱ በሣቀበት ርቃን ገላ ጥርሳቸውን አላሳዩም፤ በአምላካቸውም እንዲህ መራቆት ሀዘን ገባቸው እንጂ። ልብሶቻቸውን አውልቀው ገላውን ከለሉለት። ሀፍረቱንም ሸፈኑለት።

አምላክ የሆነውንና የሚሆነውን ያውቃልና በነቃ ጊዜ ፉጋውን ረገመው፤ እንዲህ ብሎ – “አንተ በስራኸው መሰላል ሌሎች ወንድሞችህ ይውጡበት። ከፍ ብለው ታዩበት። አንተ ግን ከመሬት ከፍ አትበል፤ እንደ ጠቆርክ ቅር፤ አትቅላ፤ ቁትህም አይሙላ…።” አለው አሉ ብለው ተረኩልኝ።

እንዳለጌታ ከበደ፣ *ኬር ሻዶ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ* (1994)



https://xtremepape.rs/

**2.**

ሲመሰቃቀል ቡርሹ
ያሳቡን አካል እያሹ
ቀለም ከቀለም እያጋባ
ሲያረግዝ የሸራው ጆርባ

አሁንም ያከዋል — ያከዋል — ያከዋል
በላኝ — ወጋኝም ሳይባል
ይደነቁለዋል — ይምሰዋል — ይጭረዋል

ግንባሩን ቋጥሮ እየፈታ
ያሳቡን ማዕበል እየገታ
ህልሙን ሞግቶ እየረታ

ተከዝ — በቡርሹ ጎንተል
ነቀል — ቆፈር — ቀለም ነከር

ይደመድመው ያወጣው እንዳለ ነገር።
ለቀቅ — ነካ ነካ ነካ
ጠቆርቆር ፈካ ፈካ
ከሸራው ላይ ክስተት
ከቀለሙ ፍጥ ነገር

ሥራውን የጎን ትቼ
የማየው ጓዴን ነበር።
እንደ ሥነ – ልቦና ሊቅ
የሂሳብ ስሌት ቀማሪ
እንደ ቀዶ ህክምና ሀኪም
ቆይቶ ጠፈር ማርማሪ

እንደ ቅኔ መምህር በእርጋታ
እንደ ትጉህ ጉጉ ተማሪ
እንደ ጸሐፌ ተውኔት ጣጣ
ገጸ – ባሕሪያት አማራጭ
እንደ አዋጊ መኮንን
የጦሩን ትልም (ፕላን) አውጭ
እንደ ጊዜው አላባሽ (ፋሽን)
ለእርቅ እንደላኩት አማላጅ
እንደ ሴቶች ፀጉር ሰሪ
ፍርድ እንደቸገረው ዳኛ

ገቢያ እንዳገኘች ኮማሪት
ወጧ እንደጣፈጠላት ባልቴት

ከጆርባው ዘንግቶኝ ቆሜ
ሲያስብ ሲባዝን ባስተውለው
ጓደኛዬ መጨነቁ ምነው?
ብዬ ላሳርፈው ስቃጣ
ላለሁ በምክር መረጣ
ድንገት ገታኝ ያ – ሸራ!!!

ምን ልበለው አበስኩ!
ዐይኔ በሰማው ደነቆርኩ
እውን የቅድሙ ሸራ
ከሙሉ አካሌ የሚያወራ?!!

አጀብ! በአጀቤ ታጀበኩ
ቀባው ልልም ጠረጠረ

ሰካው አልል ነበርኩ
አልክደው ነገር አፈርኩ
ቢቸግረኝ ዐይቶ ማመኑ
ፍርድ ጠየቅሁት ራሴኑ።
"ሸራ" አለኝ "ሸራዬ"
የሚስተናገድ እንግዳዬ

እጄ ቀለሜና ቡርሽ
የግንፍል ስሜት ቅናሽ…
"ሸራዬ!" አለኝ "ሸራ!"
የአዕምሮው መቅረዝ ጮራ!
የሀሳብ የራእዬ መጠቅለያ
ጥበብን በእጅ ማዋያ!

ሥዩም ተፈራ፣ "ታምራዊ መስኮት"፣ *ሶስቱ እንባዎች*፣ ልዋ ማተሚያ ቤት (1994)



https://xtremepape.rs/